# ሃይማኖታዊና ኢሃይማኖታዊ ዕምነቶች –ለሰባዊ መብቶችና ለማኅበራዊ ፍትኅ ያላቸው አስተዋጾ

April 11, 2024

**ሃይማኖታዊና ኢሃይማኖታዊ ዕምነቶች –ለሰባዊ መብቶችና ለማኅበራዊ ፍትኅ ያላቸው አስተዋጾ**

**ታጠቅ መ ዙርጋ**

**10–04–24**

**ማሳሰቢያ፡- 1> በዚህ ጽሁፍ ጠ/ሚኒስተር አብይ አህመድ ሳይሆን አብዲ አህመድ በሚል የተጠቀምኩት ተሳስቼ ሳይሆን ምክንያት ስላለኝ ነው**

**2> የዚህ ጽሁፍ ዓላማና ፋይዳ በቅጡ ለመረዳት በትዕግሥት እስከ መጨረሻው አንቡቡት፤ ከበፊትና ከአሁኑ የአገራችን ሁኔታዎች ጋር የተዛመደ ነው ።**

**የሃይማኖታዊ እምነትና የኢሃይማኖታዊ ዕምነት ልዩነት**

የእነዚህ አውድ እጅግ በጣም ሰፊ ሰለሆነ ፤ እጅግ በጣም ጥቅልልና እጅግ በጣም አጫጭር ትርጉማቸውን አማላክታለሁ

ሃይማኖታዊ ዕምነት /religious beliefs – ሰማይ/ህዋ፣ምድር፣ሰው፣ ፍጥረታት ወዘተርፈ ሁሉ የፈጠረ አንድ (እግዚአብሄር፣አላህ፣ጎድ) ነው በሚል ዙሪያ ያጠነጠነ ፤ የመጸሃፍ ቅዱስ ፣የቁራንና የኪታብ ትምህርት –ኢንዶክትሪኔሽን ተከታይ

ኢሃይማኖታዊ ዕምነት/UnGod centered beliefs –በጨረቃ፣ በጸሃይ፣ በመብረቅ፣ በወንዝ፣ በባህር፣በቋጥኝ ስ፣ በዛፍ፣ በተራራ፣በቋጥኝ፣ በእንስሳት፣ በተፈጥር አካባቢ ወዘተርፈ የሚያምኑ።

ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን፣እስላሞች በመስጊድ፣ ሂዱዝምና ቡዲህዝም ተከታዮች በቤተመቅደስ(በቴምፐል፣ ጁዳይዝም ተከታዮች በሲናጎግ፣ እስኪሞች በኢግሉ (ከበረዶ) በተሠራ ቤት፣ ልማዳዊ እምነት ተከታይ ፡- አፍሪካውያን፣ኤሲያውያን፣ ካርቢያውያውን ፣ሰሜን አሜሪካውያን (ቀይ ሕንዶች)፣ደቡብ አሜሪካውያን (ማያዎችና አዚቴኮች…) ፓሲፊካውያን (ፓፓኒዩጊኒዎች፣ቫንዋተዎች፣ማውሪዎች…))፣ አቦርጅኖች ወዘተርፈ –በጫካ፣በወንዝ፣በተራራ ላይ፣ በቤታቸው –ፈጣሬ ነው ብለው ከሚያምኑበት ሃይል ወይም ምስላዊ ወኪል ጋር በየቀኑ መንፈሳዊ ንግግርና ጸሎት ለማድረግ ግዜያቸውን ይሰዋሉ/ይሰጣሉ ።

ከአንጋፋው ሂዱዝም 2300 –1500 ዓ ዓ /B C ጀምሮ የሁሉንም የሃይማኖት እና ኢሃይማኖታዊ ዕምነት ዘርፎች ሶስት መሠረታዊ መርሆች ይከተላሉ ፡-

ሀ) በዚህ ምድር ላይ ይደርስብናል ብለው ከሚፈርዋቸውና ከሚያስጨንቋቸው ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቁጣዎች/አደጋዎች ይሠውሩናል፣ይከላከሉልናል ፣ ያድኑናል … የሚልዋቸውን አሳባዊ ሃይሎች መኖራቸውንና ለእነዚህ ሃይሎች መማጸን እንዳለባቸው አስረግጦ ማስተማርና መስበክ

ለ) እውነትን፣ፍትህን፣ ምግባረ ሠናይነትን ፣ደግነትን፣ ትህትናን፣ አብሮ መብላትን፣ ታማኝነትን፣ ችግረኞችን ስለመርዳትን...መስበክና ማስተማር

ሐ) የማኅበረሰቡን አባላት ፦ ከወንጀል፣ከግፍ፣ከግዲያ፣ከሥርቆት፣ከአመንዝራነት፣ከጥያፍ ሥራዎችና ከኀሊና ወቀሳ ጽድቶ መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ መምከር፣ መስበክና ማበረታታት

ሃይማኖታዊና ኢሃይማኖታዊ እምነቶች ፦ለሰው ልጅ ሁለተኛ ተፈጥሮ ናቸው ይባላል ። ሃይማኖቶችና እምነቶች ከሰው ልጅ ሕይወት ከተቆራኙበት ታሪካዊ ወቅት አንስቶ ሕዝብ ለማሰባሰብ ፣ ለማደራጀት፣ ለማንቀሳቀስ፣ ለማኅበራዊ ፍትህ (ሶሻል ጅስቲስ) ትግል ትልቅ አስተዋጾ እያደረጉ ተጉዘዋል ። ሕዝብን የማሰባሰብ፣የማንቀሳቀስና የማደራጀት አቅም እንዳለቸው ሁሉ መንግሥትን የማረጋጋት፣ በመንግሥት ላይ ለማሳመጽና መንግሥትን የማናጋት ትልቅ አቅም አላቸው ።

ሽጉጥ፣ ጠመንጃ፣ መድፍ፣ መትረየስ ፣ ታንክ ወዘተርፈ ሳይጠቀሙ ሃይማኖታቸውና እምነታቸውን የሚወክለውን ሥዕሎችና ምስሎችን ለምሳሌ ፦ መስቀል፣ ጨረቃ፣ የቡደሃ ምስል ወዘተርፈ በማንገብ ከሰፊዩ ሕዝብ ጋር በመሰለፍ (ዘረኛ፣ ፋሺስታዊ፣ አምባገነናዊና ጨቋኝ) መሪዮችና ሥርዓታቸውን ከታገሉ እና የሕይወት ዋጋ ከከፈሉ የሃይማኖትና የሌሎች እምነት ተከታይ መሪዮች ከነበሩት ጥቂቶቹ ለአብነት እጠቁማለሁ ።

- በ26 እና በ27 ዓ ም አካባቢ መጥመቁ ዮሐኒስ የእግዘብሄር መንግሥት በምድር መሆኛው ግዜ ተቃርቦዋልና ቶሎ ቶሎ ንስሃ ግቡ ብሎ ይሰብክና ተከታዮቹን በዮርዳኖስ ወንዝ ይጠምቅ በነረበት ግዜ ፤የወቅቱ የጋሊሊዮንና የፔሪያ ገዢ በነበረው 'Herod Antipas' በተባለ ሰው ትእዛዝ እንደ ተገደለ (A book of world religions–የዓለም ሃይማኖቶች)

  (E.G.Parrainder,1965) የተጻፈ መጽሃፍ ያስረዳል ።

- እየሱስ ክርስቶስ በ4 ዓ ዓ (BC) ተወልዶ በ29 ዓ ም በሰላሳ ሶስት ዓመቱ በስቅላት ሞተ ። አንዳንድ የመሃበራዊ ነጻነትና የማኅበራዊ ፍትህ (Social Libertarians and Social justice) ተመራማሪዮች – ክርስቶስ ሃይማኖት ብቻ የሚሰብክ አልነበረም፤ ሮማውያን በስቅላት የገደሉት በሃይማኖት ሽፋን– በያኔ በሮማውያን ቅኝ ሥር በነበሩ በጋሊሊዮንና በየሩሳሌም እተዘዋወረ 'እውነትን እውነት እንበል፤እውሸትን እውሸት እንበል' እያለ እስራኤላውያን የሮማውያንን አገዛዝ እንዲቃወሙና በሥርዓቱ ላይ እንዲያምጹ ይቀሰቅስ ስለነበር ነው ይላሉ ፤ የዘመኑ ማህተማ ጋንዲና ኔልሰን ማንዴላ ዓይነት ሰው ነበር ይላሉ ።

- ሳይመን ኪባጉ የቀድሞ ኮንጎ የአሁኑ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ ተወላጅና ዜጋ ነበር ። የባብቲስት ቤተክርስቲያን አገልጋይና ሰባኪም ነበር ።የምናስተምረውና የምንሰብከው የሃይማኖት ትምህርት– ከኮንጎን ሕዝብ ባህል፣ ማኅበራዊ ኑሮ፣ እሴት፣ ልማዳዊ እምነት ፣ ሥነልቦና ወዘተርፈ የተዛመደ መሆን አለበት በማለት የቅኝ ገዥ የቤልጂየምን ሃይማኖታዊ መዋቅርና አስተምሮት ተቃውሞ ማኅበረሰቡን አስተማረ አነቃ ። በመሆኑም የቅኝ ገዢዮች ፍርድ ቤት ሞት ይፍታ እስር ፈርዶበት ከ33 ዓመታት እስር በኋላ በታሰረበት እስር ቤት ሞተ ።

- በ17ኛው መቶ ክ/ዘመ አንጎላ የፓርቱጋል ቅኝ ነበር ። አንጎላውያን የፖርቹጋል የክርስትና ልዕኳን/ሚሺነሪዮች የሚሰብኳቸውና የሚያስተምሯቸው ቃልና ትምህርት እንዳለ እንዲቀበሉ እና ጥያቄ እንዳያነሱ ያስገድዷቸው ነበር ። ከዚያ ያፈነገጠ ይታሠር ፣ በእሳት ይቃጠል፣ በመስቀል ላይ ተቸክሎ ይገደል ነበር ።

'ዶና ቢትረስ' የታባለች አንጎላዊት የእነዚያ ድርጊቶች ኢሰባዊነት፣ኢፍትሃዊነትና ግፍ  በመቃወም፣የሃይምኖትና የልማዳዊ እምነት ነጻነት ለምን አይኖረንም? አፍሪካዊ ክርስቶስ ለምን አይኖረንም? አውሮፓዊ ሃይማኖትና ቄስ ለእነሱ እንጂ ለኛ ምናችን ነው? ቄስና ቅዱስ/ሴንት ለመሆን ለምን ፖርቹጋ እንላካለን? አፍሪካ የተቀደስ/የተባረከ ሰው አታፈራምን? ድንግል/ቨርጅን አፍሪካውያን የሉምን? አፍሪካዊ ደቀመዛሙርት/አፖስትልስ፣ አፍሪካዊ ክርስቶስ፣አፍሪካዊት ማርያም  ወዘተርፈ ለምን አይኖረንም? ከአንድ ሚስት/ባል በላይ አይኑራችሁ ይሉናል፣እየሱስ ክርስቶስ መቼ ከአንድ ሚስት/ባል በላይ አይኑራችሁ ብሎ ሰበከ? ባህላችንና ልማዳችን ሊያጠፉብን ነው በማለት ፍልስፍናዊና መሠረታዊ ጥያቄዎች በማንሳቷና በመቃወሟ ፤እ አ አ በ1706 ዓ ም በፐርቹጋል ዳኞች ፍርድ –በመጀመርያ ወጣት ወንድ ልጇ ቀጥሎ እናቲቱ <ዶና ቢትረስን> በእሳት አቃጥለው ገደሏቸው ። ዶና ቢትረስ አፍሪካ ካፈራቸው ጀግኖች አንዷ እንደሆነች የአፍሪካውያን ታሪክ ይናገራል ።

- ለአራት (400) መቶ ዓመታት በእንግሊዝ  ተረግጠው ከተገዙ በኋላ እ አ አ  በ1947 ዓ ም ነጻነታቸውን ያወጁትን ሕንዶች፤ በመሃተመ ጋንዲ መሪነት ፤ ጸረ እንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሲታገሉ አመጹን ያፋፋሙት –የሂንዱ ቄሶች ወይም (ፐንዲዶች)፣ የቡዲሂስት ቄሶች ወይም (ሶሞሚያዋንስ) እና ወንድና ሴት መናኩሳት ነበሩ ።

- ማርቲን ሉተር ኪንግ ፦ከእነ አባታቸው በአላባማ አሜሪካ ፣ የባብቲስት ቤተክርስቲያን ባለማዕረግ ቄስ የነበሩ ፣ 'የሰው ዘር ሁሉ በአንድነት የሚኖርበት ፣ አንድ ላይ ተቀምጦ የሚበላበት፣ የሚጠጣበ፣ የሚማርበት ወዘተ…ቀን' ይመጣል በሚል መሪ ቃል (motto) ለአመሪካ ጥቁሮች – ሰባአዊ መብቶችን፣ ማኅበራዊ መብትች፣ ፍትህ እና እኩልነትን ሲታገሉ በ1968 ዓ ም በነጭ ዘረኞች የተገደሉ።

- ጳጳስ አስካር ሮሚሮ (Archbishop A.Oscar Romero) ፦አባት ሮሚሮ ከ1917 –1980 ዓ ም የኖሩ ፣ በኤልሳልቫዶር ዋና ከተማ የሳንሳልቫዶር የኳቶሊ ቤተክርስቲያን ጳጳስ በአንድ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኝ የጸሎት አዳራሽ ውስጥ  ምዕምናንን በማገልገል እያሉ በዕለተ ሰኞ ማርች 24/1980 ዓ ም በመንግሥት ቅጥረኞች በተተኮሰባቸው ጥይት ሕይወታቸው ያጡ ።

እኚህ ቅዱስ የሃይማኖት አባት ለምን ተገደሉ?

– በድህነት የማቀቀውን፣ በበሽታ የተጠቃውን፣ በፍትህ እጦት ያለቅስ የነበረውን ወዘተርፈ የሳልሳልቫዶር  ሕዝብ ያሰማው የነበረውን ዋይታና እሮሮ አዳመጡ

– በየመንደሩ በመዞር የጎዳና ተተዳዳሪዮችን አዩ

– በየወሩ 300 ሰዎች ተገለው እሬሳቸውን – በየቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች፣ ፣ዋሻዎች፣ ጎዳናዎች፣ ጫካዎች፣ ወዘተርፈ ለአውሬ የተስጡትን እየፈለጉ ያስቀብሩ ነበር ።

– ተቀናቃኞችና የመብት ታጋዮችን ኮሚኒስት በሚል ሽፋን–ይታፈኑ፣ ይታሰሩ፣ይሶቀቁ/ቶርች ይፈጸምባቸው፣ይረሸኑ ነበር ለዚያ ተግባር አስልጣኝም ሆነ የገንዘብ ወጪ ሽፋኙ የአመሪካ መንግሥት ነበር ። ያንን ካጡኑና ከተገነዘቡ በኋላ "እኛ ክርስቲያኖች ለፍትህ፣ ለውነትና ለሕዝብ ችግር ወዘተርፈ መቆም አለብን" በማለት ጻፉ፣ ሰበኩ፣ አስተማሩ በመንግሥት ላይ ተቃውሞ አሰሙ ።

– በመሆኑም በመንግሥት ዘንድ ግራ ፖለቲከኛ አሰኛቸው ፤አጃቢና ተከታይ  እንዳይኖራቸው ቅስቀሳ አደረጉባቸው ፤ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው ፤ ይሁን እንጂ እጅ አልሰጡም ።

- ኑሮ ለጨለመባቸው ዜጎቻቸውን አቤቱታ ማዳመጣቸው፣ ለፍትህና ለስባአዊ መብት አጠንክረው መሟገትን ቀጠሉ ።
- በተለያዩ መንግሥታዊ ማስፈራርያ ዘዴዎች ቢፈተኑም አልተበገሩም ።
- ሥልጣናቸው በሚፈቅድላቸው አቅጣጫና አቅም ሁሉ የችግረኞችን መርጃ ጣቢያዎች አቁቋሙ ።
- ለአሥራ ሁለት ዓመታት ለኤልሳልቫዶር ወታደራዊ ግንባታ የአሜሪካ መንግሥት ይልከው የነበረ 1.5 ሚሊዮን ዶላር ለሕዝብ ግድያ፣ ማፈኛ፣ ስቆቃ ወዘተርፈ ይውላልና እባካችሁ አቁሙ በማለት ለፕሬዝዳንት ካርተር ጻፉ ።
- የመንግሥት–እመቃ፣ ሽብር፣ ጭፍጨፋ …እየከፋ ሲሄድ "እኔም ሕዝቤም ብቸኛ ነን ፣ አቅም አጣን በመንግሥት እየተጠቃን ነው እባካችሁ ድረሱልን" በማለት ለተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ተማጸኑ ፣ጮሁ፣ አቤቱታ አሰሙ ።
- በመቀጠልም ከማናቸውም መንግሥታዊ ስብሰባዎች ራሳቸውን አገለሉ ። ጳጳስ ሮሜሮ ዝም ለማሰኘት በተሞከሩ ማስፈራሪዎች ሁሉ አልሳካ ሲል ፣ የማሪኖል ሚሊንድ ሮፐር (Maryknol Melinda Roper) ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት የመጨረሻ ሥልጣኑን ተጠቅሞ አስገደላቸው ።

የአባት ሮሜሮ ንግግሮች ባጨሩ

"ራሳችንን በጣም መውደድ አይኖርብንም፣ ራሳችንን በጣም የምንወድ ከሆነ አደጋዎችን እንፈራለን ። አደጋዎችን ከፈራን ታሪክ ግድ የሚሉንን ሥራዎች መሥራት አንችልም ። ታሪክ የሌለው ሕይወት –ሕይወት አይደለም ። አረጌታ/ Resurrection የሌለው ሞት – ሞት አልለውም ። እኔን በመግደል ዓላማችሁን ግብ የሚመታ ከሆነ ቃል እገባላችኋለሁ ፤ ግን ትግሉን ያቃጣጥለዋል እንጂ አትገቱትም ። ብትገሉኝ በኤልሳልቫዶር ሕዝብ መካከል አርጌ/Resurrect ሆኜ እኖራለሁ ። እግዛብሄር ሰዎችን ይፈልጋል፣ ዓለምን የምናድነው ድሆች ነጻ ሲወጡ ነው ። የመንግሥትና የቤተክርስቲያን ባዶ የፕሮፓጋንዳና የሰበካ ጽሁፎች በማደል ብቻ ነጻ አናወጣቸውም ፤

ይህ ድምጻችንን የምናሰማበት የሬዲዮ ጣቢያ ቢዘጉት ፣እንዳንናገር ቢከለክሉን፣ ጳጳሶችም፣ ቄሶችም ብንገደል ፣ እያንዳ ንዱ ነብይ/prophet መሆን መቻል ያስፈልጋል ፤

ጳጳስ እስካሮ ሮሜሮ የግእግዛብሄርን ቃል በትክክል ተግባር ላይ ያዋሉ ፣ የሰው ልጅ ምድራዊ ሥቃይ ለማቃለል ተሰቃይተው የሞቱ ሃዋሬ በመባል በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት ያተረፉ የሃይማኖት መሪ ነበሩ ። ኋላም መላአክ/Saint ተብለው እተታውሱ ይኖራሉ"

➢ Father Rutilio Grande–አባት ሩቲሊዮ ግራንዴ:-እኚህ ሰው የጀሲዊት/Jesuit ሚሽነሪ አገልጋይ ቄስ ነበሩ ። ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የወንጌል ትምህርትና መልዕክት በትክክል ሥራ ላይ ለማዋል በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ወደ ሰፊው ሳልሳልቫዶር ሕዝብ አምባ ለአምባ ማለት መንደር ለመንደር ዘልቆ በመግባት አስተምሯል ፤ ሰብከዋል ። ሃይማኖትን ተመርኩዘው መንግሥት በኤልሳልቫዶር ሕዝብ ላይ ያሰፈነውን –ድህነትን፣ ግፍን፣ ጭቆናን፣ መከራን ወዘተርፈ አጠኑ፣ ተመለከቱ፣ ተገነዘቡ ። የሕዝቡን መከራና ሰቀቀን ለመንግሥት አሰሙ፣ የሥርዓቱ ኢ–ፍትሃዊነት ተቃ ወሙ ፤ተፋለሙ ። በመሆኑም በሰፊዩ ሕዝብ ዘንድ ሃቀኛ

የእግዛብሄር ሰዎች ( the true people of God) ተባሉ ። ድርጊታቸውን የወቅቱ የኤልሳልፋዶር ወታደራዊ መንግሥት ስለአስቆጣና ስለአስደነገጠ –እ አ አ መጋቢት 12/1977 ከሁለት ጋደኛሞቻቸው ጋር በመንግሥት ቅጥረኞች ተገደሉ ።

- ከአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ በደችና በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ከዚያም ከ1948 ዓ ም በዳናኤል ፈ ማላም ( Daniel F.Malam) በተመራው ዘረኛ ብሄራዊ ፓርቲ (Apartheid national party) አገዛዝ ጀምሮ ደቡብ አፍሪካው ያንን ነጻታቸውን ለመጎናጸፍ ያንን ያህል ዘመናት ታግለዋል ። የአንገሊካን ቤተክርስቲያን ጳጳስ ዴዝመንድ ቱቱ የዛ ትግል አካል በመሆን የተጫወቱትን ሰላማዊ ትግል የሉል/ዓለም ማኅበረሰብ ያስደነቀ ነበር ። የሁሉም ዘርፍ የደቡብ አፍሪካ ክርስቲያኖች በዴዝመንድ ቱቱ መሪነት፣ የደቡብ አፍሪካ እስላሞች በእነ ዶክተርዳዱ መሪነት፣ የደቡብ አፍሪካ የሂንዱ እምነት ተከታዮች በእነ ዶክተር ናኪርና ሌሎች መረነት ወዘተርፈ ይህ ቀራቸው የማይባል ትግል በመታገል የደቡብ አፍርካን የዘር መድሎ/አፓርታይድ ሥርዓት አሽመድምዷል ።

- አቡነ ጴጥሮስ ፡-ከ1892–1936 ፤ የፋሽት ጣሊያንን ወረራና ጭፍጨፋ  በአደባባ በማወዛቸው በ44 ዓመታቸው በሃምሌ 29/1936 በአደባባይ በጥይት ናዳ የተረሸኑ ሰማዕት። ..... “May GOD give the people of Ethiopia the strength to resist and never bow down to the fascist army and its violence. May the Ethiopian earth never accept the invading army`s rule” (Bishop Abune Petros). “ለፋሽስት ወታደር ለሚፈጽሙት ጥቃት ላለመምበር ከክ እግዚያብሄር ጥንካሪ ይስጣችሁ ። የኢትዮጵያ መሬት በፍጹም የወራሪ ሠራዊት አገዛዝ አይቀበልም” (አብነ ጴጥሮስ በጥይት ውርጅብኝ ተደብድበው ከመሞቻቸው በፊት) ። ማሳሰቢያ – አቡነ ጴጥሮስ በእንግሊኛ ተናገሩ ማለቴ አይደለም ። ስለእርሳቸው በንእግሊዝኛ የተጻፈ ጽሁፍ ስላነበብኩ ነው ።

- (Arch Bishop or Cardinal Fernando of philipino (የፊሊፒኖ ሊቀ ጳጳስ ፈርናንዶ):- በ1986 ዓ ም በአምባገነኑ ፈርድናድ ማርቆስ ላይ የአመጽን የማኔላ ሕዝብ፣ የኳተሊክ ቤተክርስቲያናት መሪዮች፣ ቀሳውንትና መነኩሳት በመምራት ትልቁን መስቀላቸውን ከፍ አድርገው ይዘው ወደ ቤተመንግሥት በመሄድ የማርቆስን በትረ መንግሥት ገረሰሱ ፤ማርቆ  ስም እንደ ፋሽስቱ ሃ/ማርያም አገር ተሰደደ ። የሊቀ ጳጳሱ ፍጹም ሕዝባዊ አጋርነት የዚህ ሉል/ዓልም ማኅበረሰብ አድ  ንቆታል ።
- የኢጎዝላቪያ የኦርቶዶክስ ሃይምኖት አባቶች ፡-በ2000 ዓ ም በይጎዝላቪያው አምባገነን  መሪ ሞሎሶቪችና መንግሥታቸውን ለመጣል ተቆጥቶ በተነሳው ሕዝብ ላይ –የፖሊስ፣ የጦር፣የጸጥታ ወዘተር ሃይሎች እንዳይተኩሱ፣ሕዝብን እንዳይገሉ እና ከሰፊዩ ሕዝብቸው ጋር እንዲሰለፉ በመማጸን፣ በመገወዝ  እና ከሕዝባቸው ጋር በመሰለፍ ሞሎሶፊችና መንግሥታቸውን ገረሰሱ ። ያሳዩትን ሕዝባዊ አጋርነት የዓለም ማኅበረሰብ አይቶታል
- ኔልሰን ማንዴላ፣ፋኒሉ ሃመር፣ ዶም ሄልደር ካማራ፣ ማውራ ክላርክ፣ ዶሪቲ ካዜል፣ ኢታ ፎርድ፣ኤላ በከር ወዘተርፈ  የሃይማኖት ትምህርት የቀሰሙና በሃይማኖት ትምህርት ሞያተኞች የነበሩ ፣ ፍትህና ሰብአዊ ሙብቶችን በማስከበር መር ህ የታገሉ/የሠሩ፣ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና  የነበራቸው ሰዎች ናቸው ።

**የእኛዎቹ የሃይማኖት መሪዮች ስለሃይማኖት ከመስበክ በዘለለ ፤ በአገራቸው ስለማኅበራዊ ፍትህ እጦት፣ ሰብአዊ ሙብቶች መረገጥና ስለሁለገብ ግፎች ያደረጉት ነገር አለን?**

በሃገራችን ከክርስትናና ከዕስልምና ሃይማኖቶች ውጪ በአምባገነን ገዥዮች ላይ ተጽኖ ማድረግ የሚችል/ሉ ኢሃይማኖታዊ ዕምነት ድርጅቶች ወይም ተቋማት ስለመኖር በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም። በመሆኑም ከላይ ከጠቆምኳቸው የሃይማኖት መሪዮች ሚና አንጻር፤ ባለፉት ስድሳ ዓመታት– –በአጼ ሃይለ ሥላሴ ፈራጭ ቆራጭ ዘውዳዊ አገዛዝ ፣ በመንስቱ ሃ/ማርያም ፋሽታዊ አገዛዝ እና በአክራሪ ጠባብ ብሄርተኛ የህወሃት አገዛዝ ሥርዓቶች በማህበረሰቡ ላይ ይፈጸሙ ስለበነበሩ ፡- ኢፍትሃዊና ኢስብአዊ ግፎችና ጭቆናዎች አስመልክቶ የኢትዮጵያ የክርስትናና የዕስልምና ሃይማኖት መሪዮች ሚና ምን ይመስል ነበር?

ከማኅበረሰቡ አብራክ ተወልደው በዘመናዊ ትምህርት ዓይናቸውን የከፈቱና የነቁ የሠፊው ሕዝብ ልጆች፤

–(ለማኅበራዊ ፍትህ) ማለት ሕዝባችን ተራበ፣ተራዘ፣ተጠማ፣የሚኖርበት/መጠለያ አጣ፤ስለሆነም ለጎዳና ተተዳዳሪነት ተጋለጠ፤ በወሎና በትግራይ የነበርትን ዓይነት ረሃቦች ወዘተርፈ በመቃወም

–የዳኝነትና የሕግ የበላይነት ይስፈን!የዜጎችን ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች ይከበሩ! የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ይከበር! መሬት ላራሽ! ዲሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት! የሃማኖቶች እኩልነት ይከበር! መደብለ የፖለቲካ ድርጅቶች ይፈቀድ! ዘረኛ/ አፓርታይዳዊ አገዛዝ ይወገድ ! ወዘተርፈ በማለት ሰላማዊ ትግል በማድረጋቸው ፡- ሲታሰሩ፣ ሲገረፉ፣ ሰቆቃ ሲፈጽም ባቸው ፣ ተረሽነው በጅምላ ሲቀበሩ፣በየጫካውና በየዋሻው ለአውሬ ሲጣሉ ወዘተርፈ ፤

የኢትዮጵያ የክርስትናና የዕስልምና ሃይማኖቶች መሪዮች መቃወም፣ማውገዝ፣ ይቁም ማለት፣ታቦት፣መስቀ፣ መጽሃፍቅዱስ፣የጨረቃ ምስል፣ኪታብ፣ቁራን ወዘተርፈ ተሸከመው ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት፣ ለመንግሥታት ድርጅቶች፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ወዘተርፈ ማሰማት፣አቤት ማለት፣ መማጸን ወዘተርፍ ነበረባቸው ።

ከዚያ ይልቅ ፡-የእግዚያአብሄር ቃል የሚከተል ሰው ከፖለቲካ መራቃ አለበት፣ የፖለቲካ ቃል አትተንፍሱ ብሎ በመስበክ ሕዝበ ምዕምኑ ታግሎ መብቱና ነጻነቱን እንዳያስከብር በማድረግ ፤ ከፍጹም ጨቋኝ፣ ፍሽስታዊ፣አምባገነናዊና አፓታይዳዊ ገዢዮች ጋር ተስማምተው/ኮምፐሮማይዝ አድርገው ብ ኖሩ ።

አሁንስ ምን እያደረጉ ነው? አሁን የሚገዛን ዘርኛና አምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት በትረስልጣን ከጨበጠበት 2010 ዓ ም ጀምሮ፡-

–በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሻሸመኔ፣ በጅማ፣ በወሎ፣ቢጋምቤላ፣ በቤነሻንጎል፣በጉራጌ ወዘተርፈ ኦሮሞ ባልሆነ ማንነታቸው ብዙ ሺ ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈውል፤እየተጨፉም ነው ፤ተፈናቅሎዋል፣ እየተፈናቀሉም ነው ፤ በተለይም አማሮችን ።

–በኦሮሚያ ክልል በበርካታ አካባቢዮች በርካታ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አባቶች–ተረሽነዋል፣ ታሥረዋል፣ ተገርፎዋል፣ ተዋርደዋል

–በቡራዩ፣ በሰንዳፋ ወዘተርፈ ከማፈናቀል ጋር በተያያዘ በጣም ብዙ ኦሮሞ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን ተገለዋል ፣ ከመኖርያቸው ተፈናቅሏል

– አዲስ አበባን ከከበበ (ኢንሰርክል) ባደረገ ሸገር ከተማ ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያውያን ሙቷል፣ የብዙ ሺ ኢትዮጵያውያን ቤቶች ፈርሰዋል፣ሃብትና ንብረታቸው ወድሞዋል፤ ከእነቤተሰባቸው ለጎዳና ተተዳዳሪነትና ለልምና ተዳርጎዋል ።

–በአዲስ አበባ በፈረሱና በመፍረስ ላይ ባሉ ቤተች ምክንያት 1.5 ሚሊዮን የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ከቂያቸው ተፈናቅለዋል

–ለባዕድ ከበርቴዎች ወይም የኦሮሞ ቢሊነሮችን ለማብዛት በማን አለብኝነትና በንቀት ነባር ብሄራዊ ቅርሶቻችን እያወደሙ ነው ።

–የአገር መከላኪያ ተብዬው ሙሉ ሃይሉ ተጠቅሞ – አውደ አማራ በሚኖርባቸው ሁሉ ክፍላተ ሃገራት ማህበረሰቡን (ሕጻናትን፣ወጣቶችን፣ሽማግሌዎችን፣አሮጊቶችን፣አዛውንቶችን) እየጨፈጨፈ ነው ። ስብል፣ እርሻ፣ ማሳ፣ የቀንድና የጋማ ከብቶች እያወደመ ነው ።

–ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዮች፣ ማኅበራዊ አንቂዮችን፣ ሕዝባዊ ጋዜጠኞችን፣ ሃቀኛ የምክር ቤት ተመራጮችን፣ የሥርዓቱን መሰሪነት፣ አፋኝነት፣ኢፍትሃዊነት የሚያጋልጡ ምሁራን ወዘተርፈ ወደ እስር ቤት እየተወረውሩ ነው ፤ ግርፍ፣ድብደባና ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ነው፣ ታፍነው ተወስደው ይገደላሉ ወይም መድረሻቸው አይታወቅም ።

–አውደ ሕዝቡ በቀን አንድ ግዜ መብላት ያልቻለበት፤ በሽታ ከሚገለው ሕዝብ ረሃብ የሚገለው ሕዝብ የበለጠበት ግዜ ነው ።

–አደባባይ ወጥቶ ብሶት ማሰማት፣መተንፈስ፣መቃወም ተከልክሎዋል ፤ ይህ ብታደርጉ አሳዛኝ እልቂት( ትራጀዲ) ይደርስባችኋል የሚል ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ የአገዛዝ ሥርዓት ያለበት ግዜ ነው ።

–ሁላችንም እንደምናየው ፣ የኦሮምማ ሥርዓት አንዱን ዘውግ በሌላ ዘውግ እያስነሳ ፤የአገራችንን ኅልውና በሚበታትን (ባልካናይዝድ) በሚያደርግ ሥውርና ይፋ ስልት እየሰራ ነው ፤ ወዘተርፈ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የአገራችን የሃይማኖቶች መሪዮችና ደቀመዛሙርት አንዳችም ነገር ሲያደርጉ አይታዩም ። የሌሎች ሃገራት የሃማኖት መርዮች እንደሚያደርጉት – ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት፣ ለዓለም አብያተ ቤተክርስቲያንና ለዓለም ሙስሊም ካውንስል/ሊግ፣ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ለተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት፣ለአውሮፓ ማህበር፣ ለትላልቅ ኢሃይማኖታዊ እምነት ድርጅቶች ወዘተርፈ በመጻፍ፣ አቤቱታ በማሰማትና በመማጸን የዘረኛውና የአምባገነኑ የአብዲ አህመድ አሊ የኢፍትሃዊ፣የኢሰብአዊ ፣የግፍና የጭቆና አገዛዝ ማጋለጥ ሲገባቸው ከጎኑ ተሰልፈው እሽሩሩ ሲሉት ይስተዋላል ። አገርና ሕዝብ ከሌሉ ሃይማኖት እንደማይኖር ዘንግተው ፤ ሃይማኖት ሲነካ ብቻ ሲንገበገቡ ይታያሉ ።

የአብዲ አህመድን ሁለገብ ግፍና ጥፋት አመረው የተቹ እንደ (አቡነ ሉቃስ) ዓይነቶች፣ ፖለቲካ ውስጥ ገቡ፣ፖለቲካዊ ቋንቋ ተናገሩ በሚል – በጠ/ሚኒስተር አብዲ አህመድ ደጋፊ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሹማምንት ሲተቹ ተስተዋል/ተደመጠ።

በአንድ ማህበረሰብ ሕይወት ከፖለቲካ ውጭ የሆነ ምንም ነገር የለም ። በሚበሉት ምግብ፣በሚጠጡት ውሃ፣ በሚለብሱት ልብስ፣ በሚኖሩበት ቤት ፣ የማይገባቸውን/የሚገባቸውን ለሃይማኖታዊ ማዕረግ በመሾም ባለመሾም ወዘተርፈ ውስጥ ፖለቲካ መኖሩን ስላልተገነዘቡ ይሆን?

ያ ከሆነ ወያኔ/ህወሃት በጠመንጃ አፈሙዝ አገራችንን መግዛት ከጀመረበት 1983 ዓ ም አንስቶ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አወቃቀር ፣ አሰራርና አሿሿም ዘውጋዊ አልሆኑምን? አይደለምን? ቁንጮ ቁንጮ ቦታ የያዙት ትግሬዎች አልነበሩምን? አይደሉምን? ጥቂት ሌሎች ቢኖሩም ህወሃትን የሚደግፉ ነበሩ ። ትግሬአዊ የሃይማኖት መሪዮች ፖለቲካዊ ሥራ አንቀበልም ፣ሃይማኖታዊ መምሬያ ተከትለን እንሾማለን፣እንሽራለን፣ እንሰራለን ወዘተርፈ ብለው ሞግቷለን? 'ከአህያ የዋሉች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች' ሆነና ፤ አብዲ አህመድ አሊ የኦሮሚያ ሲኖዶስ ለመፍጠር ሲሞክር የተባበሩት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መኳንንቶች ሥራ ፖለቲካዊ አይደለምን?

የኢትዮጵያ ኢስላማዊ ኡማ የተመራው ህወሃት በሚፈልጋቸው ሃይምኖታዊ ሹማምንት አልነበረምን? የአሁኑ ሙፍቲህ በኢስላሞች ጉባኤ ተመርጦ ነውን ሙፍቲህ የሆነው ? አብዲ አህመድ አሊ የሾመው የኦሮሞ ዘውግ በመሆኑ አይደለምን? ምኑ ጋ ነው ሃይማኖት ከፖለቲካ የተነጠለው ?

ሌላው ከህወሃት የአገዛዝ ሥርዓት ጀምሮ የአገራችን ሃይማኖት –የሃይማኖት መሪዮችና ሹማምንት ግላዊና ቤተሰባዊ ልዕለ ነዋይ ማካበቻ ሆኖዋል። በርካታዎች ሃማኖት የተንተራስ ከበርቴ (capitalist) እንዳሉ ይወራል ። በመሆኑ ምድራዊ ዓልም በመወደዳ ቸው ይሆን– ይህንን ጸረ አገር፣ጸረ አንድነትና ጸረ ሕዝብ የሆነን ሥርዓት ማናጋት የፈሩት?

መንግሥተ ሰማይ የምንወርሰው በምድራዊ ሕወታችን የተቀደሰ ሥራ በመሥራት ነው  እያልን ሌሎችን የምንሰብክና የምናስተምር ከሆነ– በየበረንዳው፣ በየጎዳናው፣ በየጉራንጉሩ፣ በየዕሥር ቤት ወዘተፈ ከውሻና ከአይጥ የማይሻል ሕይወት ለሚኖሩ ወገኖቻችንን ለመታደግ ታግሎ ከመሞት የተሻለ/የበለጠ የገነት በር የሚከፍትልን ቁልፍ ይኖር ይሆን?

ብጹዕ አቡነ ጴጥሮስ የተሰውበት ምክንያት (cause) በባርነት ሊገዛን በመጣ የባዕድ አገዛዝ አልገዛ በማለታቸው ነው  ። አሁን በአገር በቀል ገገር ሥር  ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ  ያሉበት ሁኔታ  –አቡነ ጴጥሮስ ከተሰውለት አገራዊና ሕዝባዊ ልዑላዊነት አደጋ ቢከፋ እንጂ ያነስ አይደለም ፤ ስለሆነም  ሁላችሁም አቡነ ጴጥሮስ መሆን ያለባችሁ ግዜ ነው! ሁላችንም አቡነጴጥሮስ መሆን የጠበቅብን ግዜ ነው !

–ሂትለረ ያን ያህል ግዜ ባይሰጠው ኖሮ የሁለተኛ ዓልም ጦርነትና የ52 ሚሊዮን ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት አይሆንም ነበር

–የፋሽስቱ መንግሥቱ አደገኛነት ከመጀርያው ኢ ሕ አ ፓ ባወቀው መጠን የኢትዮጵያ ሕዝብ አውቆት ቢያስወግዶ ኖሮ የኢትየጵያ ሕዝብ ያንን ዓይነት– ሽብር፣መከራ፣ሰቀቀን፣ፍርሃት፣እሥር፣ሰቆቃ ፣የስነ ልቦና ስብራት ወዘተርፈ  አይደርስበትም ነበር፤ በሙቶ ዓመታት የማይቶኩ እንቁ ሲቪላዊና ወታደራዊ ዜጎች አይጨፈጭፍም፣ አይመነጥርም ፣ ሬሳ አይሸጥም፣ አራት፣አምስት፣ስድስት ወዘተርፈ ልጆች የነበራቸው ወላጆች ልጅ አልባ ወይም መሃን መስለው አይቀሩም ነበር ።

–አክራሪ ጠባብ ብሄርተኛው ህወሃት ያንን ያህል ግዜ ባይሰጠው ኖሮ –ይህን ያህል ሥር የሰደደ ዘረኝነት ዘርቶ ፣አስተምሮ፣ዘውጋዊ የአስተዳደር ክልል አዋቅሮ፣ የአገራችንን የሃብት  መንጭ የራሱን ጎሳ አባላት መፈንጫ አድርጎ፣ለራሱ ጎሳ አባላት የልጅ ልጅ በሚተርፍ ሃብት አደላድሎና በዝብዞ  ወዘተርፈ አይሄድም/አይወገድም ነበር ።

–አብዲ አህመድ አሊ–በአፈጮሌነት ኢትዮ–ብሄርተኛ፣ፍጹም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ወዳድ በመምሰሉ ሠፊዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያመነታና ሳያወላው አምኖ የሰጠውን ሥልጣን በመካድ ከላይ በዚህ ጸሁፍ የጦቆምኳቸውን እኩይ ደባዎች ፈጽሞዋል፣እየፈጸመም ይገኛል ። ባለፉት ስድስት ዓመታት በብልጽግና ጭንብል/ማስክ ሽፍኖ የኦሮምማ ሥርዓት ለማስፈን ካልሆነለትም ኦሮሚያን ለማስገንጠል ያልፈነቀለው ድንጋይ፣ያልዘየደው ዘዴ የለም ።   በተግባር እንዳየነው  ሁለገብ የአገራችንና የሕዝባችንን  ሕልውና ከድጡ ወደ ማጡ ፣ከጤናማነት ወደ አደገኛነት አምርቷል። የአገራችንና የሕዝባችንን መጻኢ ዕጣ ወደ ቁጣ ወይም ማዓት ከማምራታቸው በፊት ይብቃህ! ዞር በል ማለት ግድ ይለናል ። ያቀደውንና የተለመውን ጥፋት ካጠናቀቀ በኋላ መጸጸትና መቆጨት ጀብ ከሄድ ውሻ ጮኸ ይሆናል ።

በመሆኑም –ፓትራርኩ፣አቡኖቹ፣ ጳጳሳት፣ቀሳውስት፣ መነኩሳት፣ ዳቁናት ታቦት ተሸከመውና መስቀል ይዘው ፤ሙፍቲህዮች፣ ኢማሞች ፣ ሼካዎች፣ደረሳዎች፣ሙሳፊሮች ፣ሃጂዎች፣ፉቀራዎች ወዘተርፈ የጭረቃ ምስሎችና ሌሎች ሃይማኖታቸውን የሚፈቅድ ነገሮች ይዘው  የሌሎች አገሮች የሃማኖት መሪዮች እንዳደረጉት ፤ሰፊዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመምራትና  እጅ ለእጅ፣ ትከሻ ለትከሻ፣ ክንድ ለክንድ ተያይዘን ፣ሥነልቦናችንን አገናኝተን –በማመጽ ይህ ጉግ ማንጉግ የአፓርታይድ ሥርዓት ከነግሳንግሱ መንግለን በመጣል አገራችንና ሕዝባች ነጻ ከማውጣትና ከማስከበር ሌላ አማራጭ የለንም ! ሌላው አማራጭ ለውርድትና በአገር በቀል ቅኝ አገዛዝ መገዛት ነው ።

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ባወቃቸው ጀግናና አይበገሬ ልጆቻቸው ተከብረው ይኖራሉ !!

- አው ሃይማኖቶችና  ኢሃይማኖታዊ እምነቶች ለማኅበረስብ/ለሰዎች  –እምባ፣ መከራ፣ ሰቆቃ፣ብሶት፣ስቃይ ወዘተርፈ ጥብቅና መቆም አለባቸው ። ስለሰማይ ቤት ሕይወት ብቻ መሰበክ አይበቃም/ፋይዳ የለውም ።

- የእግዚአብሄር መንገድ፣ የጌታ እየሱስ ቃል፣ የነብዩ ማሃመድ ቃል፣ የመጽሃፍ ቅዱስም ሆነ የቁራንና ኪታብ ትምህርት ስንሰብካቸውና ስናስተምራቸው –ቁሞ የመስማትና የማዳመጥ አቅም አላቸውን? የሚውሉበት፣ የሚያድሩበት፣ ከጸሃይ፣ ከዝናብ፣ ከብርድና ከውርጭ የሚጠለሉበት፣ጎናቸውን የሚያሰርፉበት ቦታ አላቸውን?

- የሚበሉት፣የሚቀምሱት፣ የሚጠጡት ውሃ ፣ የሚቆረጠም ጥሬ ወዘተርፈ ያገኛሉን? ብለን እንጠይቃለን?

- በሕዝባችን ላይ የተጫነው ፡-ረሃብ፣ርዛት፣ ጥማት፣በሽታ፣ ድንቁርና፣ ጎዳና አዳሪነት፣ ጉስቁልና ወዘተርፈ ምክንያት (cause)ምንድ ነው ? ከየት መጣ ? ከፈጣሪያችን ከሰማይ የወረደ ወይስ በገዢዮቻችን ብልሹ አስተዳደር ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን ?

- የተቀደሰ ሥራ በመስራት መንግሡተ ሰማይ እንወርሳለን እያልን ለሌሎች የምንሰብክ ከሆነ –በየበረንዳው፣ በየጎዳናው፣በየጢሻው፣ በየጉራንጉሩ፣ በየዕስር ቤት ወዘተፈ ከውሻና ከአይጥ የማይሻል ሕይወት ለሚኖሩ ወገኖች ለመታደግ ታግሎ ከመሞት የተሻለ የተቀደሰና የገነት በር የሚከፍት ቁልፍ ይኖር ይሆን ።

- የሃማኖትና የኢሃይማኖት እምነት መሪዮችና አገልጋዮች የማኅበረሰቡ ምድራዊ ኑሮ ያስቀደሙ ወይም ያማከሉ መሆን አለባቸው ባይነኝ ፤ እንደዚያ ከሆነ የሃይማኖትና የዕምነት ድርጅታቸው ተወዳጅ ይሆናል፤ ተቀባይነት ይኖሮዋል ። ያ ባለመሆኑን የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱንም ሃይማኖቱም የሚጠላበት ደረጃ ደርሷል ።

To leave a comment, click the button below to sign in with Google.

SIGN IN WITH GOOGLE

## Popular posts from this blog

### በአዲስ አበባ ቆይታዬ ከአየኋቸው በርካታ ችግሮች ጥቂቶቹ

*December 22, 2023*

በአዲስ አበባ ቆይታዬ ከአየኋቸው በርካታ ችግሮች ጥቂቶቹ ታጠቅ መ ዙርጋ፤ 22/12/23 ይህ ስል ሞላ አ/አበባ አዳረስኩ ማለቴ አይደለም። ስለ አ/አበባ ጥናትና ምርምር አደረኩ ማለቴም አይደለም ። በቃጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትኛውም አገር ማኅበረሰብ ሕይወት ከፖለቲካ ጋር የተዛመድ/የተያያዝ ነው ። ስለሆነም በአዲስ አበባ ቆይታዬ ያየኋቸው ስል ከቀጥታ ከአገራች …

READ MORE

---

### በትህነግና በኢት-ሕዝብ መካከል ስለተደረገ ጦርነት

*January 09, 2024*

በትህነግና በኢት - ሕዝብ መካከል ስለተደረገ ጦርነት ታጠቅ መ ዙርጋ = 09/01/24 በትህነግና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ስለ ተ ደረገው ጦርነት በዲያስፖራ ከሚኖሩ ተጋሮች ጋር ክርክር ሲደረግ ለመከላከ ለ (defence mechanism) የሚያ ቀርቧ ችው ነጥቦች ፡- 1) ጦርነቱ የተከፈተው በትግራይ ሕዝብ ላይ ነበር። ትህነግ ባይከላከል /ባይመክት ኖሮ የት …

READ MORE

Powered by Blogger

Theme images by Michael Elkan

TATEK ZURGA

VISIT PROFILE

Archive

Report Abuse